ኢኽላስ የዳዕዋ ክበብ

ikhlasjemaa@yahoo.com

# ቀለማትና ኪታቦች

"ወዲኒ ነቢ"፣ "ነብያችንን"፣ "ቁርአን ለምታልህ?"፣ "ቁርአንን"፣ "የቁርዐን በረካ ይድፋኝ"፣ "አባቴ ይሙት"፣ "ከእናቴ ስጋ ይነጥለኝ"፣ "የእናቴን ቀን ያሳየኝ" ...... ሉፍፍፍ ሲዘገንን ያ አሳህ! እነዚህ ሁሉ የልጅነት ማሀላዎቻችን ነበሩ:: የሆነን ነገር ፈልገህ ሰው ስትለምን ደግሞ "በ 30 ጁዝ ቁርዐን"፣ "በነብያችን"፣ "በእናትህ"፣ "በአከሌ" ምናምን ትለውና ግግም ሲል "በሁሉም ይዤሀለው" ብለህ ጥፍር አድርገህ ታስረዋለህ:: የት አባቱ ይሄዳል? "በሁሉም" ተይዞ! እንዲህ ነው እንጂ:: ዛሬ አድገናል እንበል (አርጅተናል ማለት ይብሮኝ ነው)፥ ማሀላችንም በቁጥርም በአይነትም አድጓል:: ትላንት በ"ሁሉም" ብለን በያፈናው የማልንባቸው አካሎች ዛሬ "ስፔሺያላይዝ" ስናደርግ ለብቻ ለብቻ ነጣጥለን እንደ ጉዳዩ ክብደት አስፈላጊውን አካል ጥቅም ላይ ማዋል ጀምረናል:: "ጌታው ሸህ አሊን እንዲህ አላልኩም"፣ "አብዶዬን እኔ አይደለሁም"፣ "አባቴ ይድፋኝ እንዲህ አልወጣኝም" ....ዋ ኢስላማ!.... እንዴ በአገሩ "ወላሂ" ብሎ የሚምል የለም ማለት ነው? ተው ተው! አስ አትችኩል! ግባ መርካቶ፥ ዱባይ ተራ ቦምብ ተራ፥ እዛ ደግሞ መሀላ የአረፍተነገር መባቻ ሆኖ እስክትመግብ ድረስ ስምተህ ትመለሳለህ:: ሰዉም እኮ ተላምዶት ልክ እንደ ዝንብ ከወፎችህ መሀል "ወላሂ ወላሂ" የምትለውን "እሽ እሽ" እያለ ነው የሚያዳምጥህ:: ለማንኛውም መሀላ ቁምነገሩ "Made in China" የሚለውን ጽሁፍ ማስለቀቅ አልነበረም:: በጭራሽ! ባይሆን ለምትምልበት አካል ያለህን ፍራቻና ክብር ይገልጻል:: አድማጭ ሆነህ ከተማለልህ ደግሞ በተማለበት አካል ያለህን እምነት ያህል ተናጋሪውን ታምነዋለህ ማለት ነበር:: አስር ግዜ "ወላሂ" አስብለኸው "እስቲ እጁን ምታልኝ" የምትለው አንተ የትኛው አጣሪ ኮሚቴ ነህ? እንተማመን እንጂ ጎበዝ! አውቃለሁ ልማድ ሆኖብኝ ነው እንደምትለኝ:: ወደ ቤትህ ግባ ደግሞ:: ከዛ አንድ በእድሜ ተለቅ ያለ ሰው "ሽኮቼን፣ ቀሴዬን፣ ጨለዬን" እያለ ሲያላምን ትሰማለህ:: አንተም ቀብበል ታደርግና "እንዴ ይሄ ነገር እኮ ሽርክ ነው አባዬ!" ማለትህ አይቀርም:: ወሬ አዳማቂውም ሳትቀድመው "ኢዲያ እሄ ነጭ ኪታብ አያመጣው የለ!" ይልና ርእሱን ወደ ቀለማት ምርጫ ይቀለብሰዋል:: ከመቀጽበትም የአንተ አፍ ሳይከተ የእነርሱ ጆሮዎች ይዘጋሉ:: ከእቤት ስትወጣ "ወሀቢይ" ይሉሀል፥ እቤት ስትሆን ደግሞ "ኪታብህ ነጭ ነው" ነው ሙግቱ:: ወይ አበሳ ... እውነት ግን ኪታብህ ቀለሙ ምንድነው? አሁን ድረስ የሚያናደኝ ደግሞ ምን መሰለህ .... ቆይ አንተ: "ትልቅ" ሰው ናቸው "ጉልበታቸውን" ሳም ተብለህ አታውቅም? እርግጠኛ ነኝ አጋጥሞሀል:: ከዛ ያቺ ሚጢጢ ጉንጩን በአንድ እጃቸው ጨምድደው ይይዟትና አፋቸው ውስጥ ያለውን የ"ጫት" መረቅ ፊቴ ላይ ይነሰንሱብኛል:: ትምህርት እንዲገባኝ፥ ሹመት እንዳገኝ፥ ሀብታም እንድሆን እኮ ነው አረፍ አይደል! ለአኼራውማ ጡሴዬን ይዘህ ተከተለኝ ብለውኛል:: ..... እንዲህ እየተባልን ከስንቱ "በረካ" ዛቅን መሰለህ:: ሌላ ደግሞ በመስጂድ ማይክራፎን ከሚነገር ታሪክ አንዱን ላውጋህ:: ዝናብ ጠፋ አሉ የሆነ አገር እና ሰዉ በጣም ተጨነቀ:: ከዛ መላ ሲያስፈልጉ ከቆዩ በኋላ ወደ አንድ ታዋቂ ወደሆነ ቀብር ዘንድ ሄዱ እና ጉዳያቸውን አጫወቱት:: ሟችም ግራ ቀኙን በጥሞና ካጤነ በኋላ: "ጋቢያችሁን ዘርጉና ንግግሬን እፈሉ፥ ከዛም መልሳችሁ ቋጥሩት፥ አገራችሁ ሳትደርሱም እንዳትፈቱት" ብሎ ይነግራቸዋል:: ሰዎቹም እንደተባሉት አገራቸው ሲደርሱ ጋቢያቸውን ክፍት ቢያደርጉት ወዲያውን አገሩ ዝናብ በዝናብ ተጥለቀለቀ ይባላል:: (ሙሉውን ታሪክ "ለማ በገበያው" የሚለው የ4ኛ ክፍል አማርኛ መጽሀፍ ላይ ይፈልጉት):: አላህ ያላያችሁ እስቲ ይሄ ተረት ተረት መስጂድ ውስጥ ይነገራል? ዛሬ ሰዎች "በረካ"ን ፍለጋ ድንበር ለቀው ከንፈዋል:: ከዛፍ፣ ከሙዳይ፣ ከድንጋይ፣ ከገዳላት፣ ከቀብር ቦታዎች፣ ከቀናቶች እንኳ ሳይቀር ማለቴ ነው:: ሌሎች ደግሞ የህብረተሰቡን ድክመት አይተው በየሀድራው እንደ የጆባታው መጠን "በረካ" የሚቸረችሩም አሉ:: ሰዉም አይኑ ተይዞበት ኖሮ በየቂምሀው መሀል "በርክ" ሲል ያጋጥምሀል:: እኔ እኮ ማይገባኝ ለኛ "በረካ" ሳምታቿዎቹ "ፈረንካ" ይሁን ያለው ማን ነው? ቀድሞውንስ "በረካ"ውን ሸጠኸው "ፈረንካው" ምኑ ይረባሀል? ባይሆን አንድ ክስተት ትውስ አለኝ:: እየውልህ በአንድ አጋጣሚ ላይ መልእክተኛውን صلى الله عليه وسلم አዳዲስ ሰለምቴዎች ይመጧቸውና እንደ ሙሽሪኮቹ ሁሉ ለእኛም "በረካ መጎናጸፊያ" ዛፍ ያብጁልን ይሏቸዋል:: ያን ግዜ የነበረውን የነብዩን ቁጣ ይሄን ያህል ነው አልልህም፥ ግን ምን አሉ መሰለህ "....... !الله أكبر" ::

የከባድ ቁጣ ማሳደያ ቃል:: አዎን እጅጉን ተቆጡ ሙስጠፋ صلى الله عليه وسلم :: ጉዳዩ መርዝ ነውና:: እኔ አሁንም እቤትህን ፈትሽ ነው ምክሬ:: ወላጆችህ ዘንድ ዝለቅና "አንታለል"፥ "ጉዳዩ ከባድ ነው"፥ "ከእስልምና ያስወጣል"፥ "በፈካውም ቢሆን በአላህ እጅ ነው" በላቸውማ .... የእነርሱ መልስ እንደሚከተለው ይሆናል:: በፊት በብላክ ቴሌቪዥን ዘመን ከጎረቤት ልጆች ጋር ተጋፍተን ኳስ ጨዋታ ድጋፍ ስንሰጥ ገሚሳችን የ"ነጭ" ስባሽ ገሚሳችን ደግሞ የ"ጥቁር" እንሆን ነበር:: ምንም አይነት ቀለም ያለው ምስል ቢመጣ እኛ ጋር ነጭ ወይንም ጥቁር ሆኖ ነበር የሚታየን:: ሌላ አይነት ቀለም የምናየው ምናልባት "ስዕል" ደብተራችን ላይ ብቻ ነው:: ከዛልህ የእድል ነገር ሆኖ ከለር ቲቪ በየሰፈሩ ነገሰ፥ በመሆኑም የኳስ ተጨዋቾቹ ቁምጣና ካልሲ እንደሚለያይ ተደረሰበት፥ ህጻናቱ ሁላ ቀለም ይጽፋ፣ ቀለም ይገባቸው፣ ቀለም ይታያቸው ጀመር፥ ወላጆቹ ግን አሁንም ድረስ "ነጩ ኪታብ" ማለት አላቆሙም:: አላህ ይዘንላቸው ማጠቃለያ  ተከትለኸኝ እንደሁ በሁለት የተለያዩ ርእሶች ስር አንድ አምስት ነጥቦችን ባልተገራ አማርኛ አዉጋዉህ ከሆነ ከአጥር ጀርባ ከተወረወረ መጽሀፍ ኮርጁ ማለት ነው:: ባለቤቱ ግን ከስድሳ በላይ ቁምነገሮችን በአንድ ታዋቂ ርእስ ስር አካቷቸዋል:: የሆነው ሆኖ ኋላ ላይ ማንነቱን እጠቁምሀለው:: ያለንበትን ግዜ በአንጻሩም ቢሆን የ"በረዶ ዘመን" እለዋለሁ:: ሙስሊሞች የሚወያዩበትን አንድ መስኮት ብትከፍት አልያም ስለ ሙስሊሞች ዜና ታትሞ ብታነብ ብሶት እንጂ አያጋጥምህም:: መቀሌ፥ ጎንደር፥ ሀረርጌ፥ አወልያ፥ በኒ፥ ሶሪያ፥ የመን፥ ኢራቅ፥ ፈረንሳይ፥ ፓኪስታን .... አያሌ በርካታ ቦታዎች:: በልሒታዎች ሁሉ ዙሪያችንን ከበው ካማራቸው ቦታ ይቦጫጭቁናል:: ሲፈልግ በ"ወሀብያ" ሹካ እንደ ፓስታ ይጠቀልሉናል፥ ካልሆነም እንደ ቁርጥ ስጋ በ"አሸባሪ" ቢላ ጎረድ ጎረድ ያጫውተናል:: እንዳው ካማራቸው ቦታ አልኩህ እኮ:: ለማንኛውም ከዚህ የላቀ የ"በረዶ ዘመን" እፊታችን ቆሟል:: ለዛን ግዜ ከበጀህ ብዬ ነው ስለ በረዶ ዘመን ቃልኪዳኖቹ ማውራቴ:: ነገሮች ሁሉ እንዲህ ምስቅልቅል ባሉብን ሰአት ማምለጫ አቋራጩ ራስን ዞር ብሎ መፈተሽ ብቻ ነው ባይ ነኝ:: ከአላህ ተጣልቶ "መፍትሄ አፋልጉኝ!" ማለት መታወር ይመስለኛል:: ነገ ደግሞ እኮ አላህ ፊት መቆም አለ፥ ስለ ቃልኪዳኖቹ መጥጠየቅም አለ፥ ስራዎችን ማስመዘንም አለ፥ ነፍሱንም በሽርክ የበደለ ሰው በደለኛ የሚሆንበት ፍርድም አለ እኮ ዘመዶቼ:: አንዳንድ ግዜ ግፍ እንዲህ መብዛቱን ሳስተውል "ምናለ አሁኑኑ ቂያማ ቆሞ ቢለባቸው!" ብዬ እመኝና ደግሞ የነፍሴ በደሎች ትዝ ይሉኛል:: ዳሩ በማናችን በደል ቀድሞ እንደሚፈረድ ከቶ ማን አወቀው? የእኔ በደል በነፍሴ ላይ ወይንስ የጠላቶቼ በእኔ ላይ? አላህ ይሁነን ብቻ:: መልካም! "በዚህ ፍጥነት ቢመጡን እንኳ?" ነው የሁላችን ጥርጣሬ: አይደል? አዎን ጠላት የከነፈውን ያህል ቢከንፍ ከአላህ ጋር የተውሂድ ፍቅር ስመመስረት እንቅፋት አይሁነን:: ያለ ጠላትም እኮ መሰቃየት፣ መንገላታት አለ፥ መታመም፣ መሞት፣ መቀበርም አለ፥ ያለ ተውሂድ ግን ሁለቱም አገር ላይ ቅንጣት ህይወት የለም:: "ለእርሱ ገሀነም አለችው፡፡ በውስጧም አይሞትም ሕያውም አይኾን" ይላል መመሪያችን:: እናም ዛሬ ስተገፋው ሰውነታችን ነገ ማረፍያ የሚሆን ቦታ እናብጅለት ወገን:: በአጠቃላይ የሰጠሁህ አምስት ቃልኪዳኖች ላይ ሀምሳ ምናምን ስትጨምርበት አንድ ዝነኛ መጽሀፍ ታዘጋጃለህ ማለት ነው:: አባዝተህ፥ ተርጉመህ፥ አብራርተህ አስረዳቸው ቤተሰቦችህን፥ ከቻልክም አሰራጨው:: ሰዎችንም አንብቡት ከምትላቸው ብታነብላቸው ይቀላቸዋል --- እንዳይሰሙ እንዳያዩ ሆነው የታሪክ ማእቀብ ተጥሎባቸዋልና:: በነገርህ ላይ ስለ ርእሱ ብዙ አትጨነቅ፥ ዋናው መልእክቱን አድርስ እንጂ የፈለግከውን ሰይመው:: ካላገኘህም እኔው ልጠቁምህ:- ....................."كتاب التوحيد لشيخ الإسلام محمد ابن عبد الوهاب"...................... ልትለው ይመችሀል:: ጨርሻለሁ:: جعلني الله وإياكم ممن ذُكِّر فنفعته الذكرى وصلى الله على محمد وعلى آله وصحبه وسلم